የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፶፩
አዲስ አበባ ሰኔ ፴ ቀን ፲፱፻፹፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

3rd Year – No. 51
ADDIS ABABA, 7th July, 1997

## ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፲፰/፲፱፻፹፱ ዓ.ም.
የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ................................ ገጽ ፮፻፲፩

## CONTENTS

Council of Ministers Regulation No. 18/1997
Ethiopian Electric Power Corporation Establishment Regulations ..................................... Page 611

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፲፰/፲፱፻፹፱ ዓ.ም.
### የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽንን ለማቋቋም የወጣ ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ በአንቀጽ ፵፯/፩/ሀ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፲፰/፲፱፻፹፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· <u>መቋቋም</u>

፩· የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን (ከዚህ በኋላ "ኮርፖሬሽኑ" እየተባለ የሚጠራ) የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

፪· ኮርፖሬሽኑ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል።

፫· <u>ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን</u>

በመንግሥት የሚሰየም አካል የኮርፖሬሽኑ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል።

### Council of Ministers Regulations No. 18/1997
### REGULATIONS TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE ETHIOPIAN ELELCTRIC POWER CORPORATION

These regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/1995 and Article 47(1) (a) of the public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

1. *Short Title*

   These Regualtions may be cited as the "Ethiopian Electric Power Corporation Establishment Regulations No. 18/1997"

2. *Establishment*

   1. There is hereby established the Ethiopian Electric Power Corporation (hereinafter the "Corporation") as a public enterprise.
   2. The Corporation shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

3. *Supervising Authority*

   A body to be designated by the Government shall be the Supervising Authority of the Corporation.

፬· ዋና መሥሪያ ቤት

የኮርፖሬሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ሊኖረው ይችላል ።

፭· ዓላማ

የኮርፖሬሽኑ ዓላማ (በመንግሥት ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ የልማት ፖሊሲዎችና እቅዶች ላይ በመመርኮዝ) የኤሌክትሪክ ኃይል ማምረት፣ ማስተላለፍ፣ ማከፋፈል እና መሸጥ፣ በተጨማሪም ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን መሥራት ነው።

፮· ካፒታል

ለኮርፖሬሽኑ የተፈቀደለት ካፒታል ብር ፮ ቢሊዮን ፩፻ ሚሊዮን (ስድስት ቢሊዮን አንድ መቶ ሚሊዮን ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፪ ቢሊዮን ፮፻፸ ሚሊዮን (ሁለት ቢሊዮን ስድስት መቶ ሰባ ሚሊዮን ብር) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል።

፯· ኃላፊነት

ኮርፖሬሽኑ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም።

፰· ኮርፖሬሽኑ የሚቆይበት ጊዜ

ኮርፖሬሽኑ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል።

፱· የመብትና ግዴታ መተላለፍ

በመንግሥት ማስታወቂያ ቁጥር ፪፻፲፫/፲፱፻፵፰ መሠረት ይተዳደር የነበረው የቀድሞው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ መብራትና ኃይል ባለሥልጣን መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኮርፖሬሽኑ ተላልፏል።

፲· ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሰኔ ፴ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ሚኒስትር



4. *Head Office*

The Corporation shall have its Head Office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere, as may be necessary.

5. *Purpose*

The purpose of the Corporation is to engage in the business of producing, transmitting, distributing and selling electrical energy (in accordance with economic and social development policies and priorities of the Government) and to carry on any other related activities that would enable it achieve its purpose.

6. *Capital*

The authorized capital of the Corporation is 6.1 Billion Birr of which 2.67 Billion Birr is paid up in cash and kind.

7. *Liability*

The Corporation shall not be liable beyond its total assets.

8. *Duration*

The Corporation is established for an indefinite duration.

9. *Transfer of Rights and Obligations*

The rights and obligations of the Ethiopian Electric Light and Power Authority established under General Notice No. 213/1956 are hereby transferred to the Corporation.

10. *Effective Date*

*Done at Addis Ababa, this 7[th] day of July 1997.*

*MELES ZENAWI*

*PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA*